በ2008 ዓ.ም መባቻ ላይ የተካሄደውን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ለውጥ ተከትሎ በክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮና በገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የስልጣንና የኃላፊነት ድልድል ይበልጥ ለማጥራት ይቻል ዘንድ በስራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHERE AS ,it has been found necessary to revise the Proclamation No 230/2015 to scrutiny more the rendered powers and responsibilities between the regional road and transport bureaus and the rural roads construction agency following to the organizational change of the national regional state executive bodies,

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 49 ንኡስ አንቀፅ 1 (3) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the council of Amahra Region in accordance with the powers vested in it under sub-article 3(1) of Article (49) of the revised national constitution, the region hereby issued this Proclamation.

## 1. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ *"የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 248/2009 ዓ.ም"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Revised Executive Bodies' Establishment Proclamation Amendment Proclamation No 248/2017.''

## 2. ማሻሻያ

የተሻሻለው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥቱ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፦

## 2. Amendment

The Revised Amhara National Regional State Executive Bodies' Establishment, Organization and Determination of their Powers and Duties Proclamation No 230/2016 is revised by this Proclamation as follows:

በአዋጁ አንቀፅ 18 ከንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ ንኡስ አንቀፅ (5) የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ መግባት ምክንያት ከንኡስ ንቀፅ (5) እስከ ንኡስ አንቀፅ (30) ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ከንኡስ አንቀፅ (6) እስከ ንኡስ አንቀፅ (31) ሆነው ወደፊት ተሸጋሽገዋል።

5. የገጠር መንገዶችን ግራና ቀኝ ተዋሳኝ አካባቢዎችን ጨምሮ ለመንገድ ግንባታ የሚያስፈልገውን የመሬት መጠን በየጊዜው እያጠና ስልጣን ላለው የክልሉ መንግስት አካል በማቅረብ ያስወስናል፣ መሬቱ የግለሰብ ፣ የቡድን ወይም የድርጅት ህጋዊ ይዞታ ከሆነ ደግሞ እንደ አግባብነቱ ለመሬቱ ትክ ቦታ እንዲሰጥና ወይም በመሬቱ ላይ ላረፉ ወይም ለሚገኙ ንብረቶች በህግ መሠረት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

## 3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕርዳር**

**ጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓ.ም**

**ገዱ አንዳርጋቸዉ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት**

The following new sub-article (5) stipulated here in under is incorporated next to sub-article (4) of article 18. Due to the incorporation of this additional provision, the provisions from sub-article (5) up to sub-article (30) are arranged from sub-article (6) up to sub-article (31) for ward.

**5**. Submit to the authorized regional government for approval by studying periodically the extent of land required for road construction activities including the adjacent surrounding of rural roads, and if the land is a legal land holder of an individual, team or institution; properly make a suitable condition for the land to be replaced and /or/ appropriate compensation to be paid for properties placed or found on the land in accordance with law.

## 3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come in to force as of the official date of its publication in the Zikre –Hig Gazette of the regional state.

**Done at Bihar Dar,**

**This 3rd Day of November, 2017.**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Regional State**